# የማንነት ፖለቲካና መፍትሄው (ከይገርማል)

ማንነቶች የአንድን ግለሰብ/ማኅበረሰብ አኗኗር፣ አሰራር፣ አስተሳሰብ፣ እምነትና ልማድን የሚያሳዩ ባህሪያዊ እና አካላዊ መገለጫዎች ናቸው። ማንነት ከግለሰብ ይጀምራል። አንድን ሰው ማን ነህ ሲሉት ሊናገር የሚችለው በራሱ ዙሪያ ስላለው ነገር ነው። እከሌ እባላለሁ ብሎ ይጀምርና ስለ ዕድሜው፣ ስለሚከተለው ዕምነት፣ ስለትምህርት ደረጃው፣ ስለተሰማራበት ሙያ፣ ስለማግባትና አለማግባቱ፣ ስንት ልጆች እንዳሉት፣ የት እንደሚኖር ይገልጻል። ይህን አይነት ማንነት የግለሰብ ማንነት ብለን እንወስደዋለን። ግለሰባዊ ማንነት ከማንኛውም ሰው ጋር የሚጋራቸው ሰብአዊ ማንነቶች እንዳሉት ሁሉ የግል አካላዊና ባህሪያዊ መለያወች አሉት።

ሁለተኛው ማንነት ቤተሰባዊ ማንነት ነው። ቤተሰባዊ ማንነት የቤተሰብ አባላቱን ግለሰባዊ ማንነት የሚያጠቃልል ሆኖ ይገለጻል። ቤተሰባዊ ማንነት በአባትና በእናት በኩል ያሉትን ልዩነቶች በአንድ አስተሳስሮ ለልጆች ግለሰባዊ ማንነት መሰረት የሚጥል በሕብረተሰብ አደረጃጀት ውስጥ የመጀመሪያው እርከን የሆነው ቤተሰብ መገለጫ ነው። እንደግለሰባዊ ማንነት ሁሉ ቤተሰባዊ ማንነትም አንዱን ቤተሰብ ከሌላው ቤተሰብ አንድ የሚያደርገው እና የሚለየው ከደም ትስስር ያለፈ የራሱ ባህሪ ይኖረዋል። የአንዱ ቤተሰብ የአስተዳደር እና የአኗኗር ዘይቤ ከሌላው ቤተሰብ የአስተዳደርና የአኗኗር ዘይቤ የሚለይበት ብዙ ነገር አለ።

ሦስተኛው ማንነት አካባቢያዊ ማንነት ነው። በዚህ ማንነት ውስጥ የሚጠቃለሉ ሰዎች በቋንቋ፣ በሀይማኖት እና በቀለም የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ባሳለፉት የረጅም ጊዜ መስተጋብር የሚወራረሷቸውና በጋራ የሚያኅለብቷቸው ማንነቶች አሉ። በአካባቢያዊ ማንነቶች ላይ የሚታዩት የጋራ እሴቶች ላይ ባህላዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ልማዳዊ እና ስነልቦናዊ አንድነቶች ይንጸባረቃሉ። አካባቢያዊ ማንነቶች የግዛት አንድነትን ተከትሎ አካባቢን በማልማትና በመከላከል ከላብ እስከደም የሚጠይቁ ተግባራትን በጋራ በማከናወን የሚፈጠር ትስስር በመሆኑ እንዲህ በቀላሉ የሚበጠስ አይሆንም። የወልቃይት እና የራያ ጥያቄ በረጅም ጊዜ አብሮነት በተፈጠረ የአካባቢያዊ ማንነት ላይ የተገነባ ስለሆነ ወደቀድሞው ማንነታቸው እንዲመለሱ ካልተደረገ በስተቀር በማባበል፣ በማታለል፣ በማስፈራራትም ሆነ በማስገደድ ባልለመዱት ክልል ውስጥ ተጠቃለው እንዲቀጥሉ ማድረግ አይቻልም።

ሌላው ማንነት ሀገራዊ ማንነት ነው። ይህ ማንነት የሁሉንም አካባቢወች ልዩነቶች አቻችሎ በማስቀጠል የጋራ ሀገራዊ እሴቶችን የፈጠረ ማንነት ነው። ሀገራዊ ማንነት ሀገርን በመከላከል፣ በአስተዳደር፣ በብሔራዊ በአላት፣ በሰንደቅ ዓላማ፣ በብሔራዊ መዝሙር፣ - - - የሚገለጽ ቁርኝት ሲሆን በፓርላማ፣ በመከላከያ ኃይል፣ በሀገር ደህንነት እና ጸጥታ ጉዳዮች በሚኖር የጋራ ተሳትፎ ቁርኝቱን ፍትሀዊ በማድረግ የሚቀጥል ይሆናል። ፍትሀዊ አሰራር እንዲኖር ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ስርአት መስፈን፣ የራስን በራስ የማስተዳደር መብት መከበር፣ የዜጎች ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ የመኖር እና የመስራት መብት መረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል።

በዓለም ላይ የሚኖሩ የተለያዩ ሀገራት ሕዝቦች በየሀገራቸው ከሚኖሩ የዜግነት ተጋሪወቻቸው በተለየ ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚጋሯቸው ማንነቶች እንዳሉ ማወቅ ተገቢ ነው። ለምሳሌ የቆዳ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት አንዱን ክፍለዓለም ከሌላው ክፍለዓለም የሚያስተሳስር ሆኖ በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉትን ሰዎች ግን የሚያለያይ ሊሆን ይችላል። በሀገራችን የሚኖሩ ክርስቲያን እና ሙስሊሞች በሐይማኖት አንድ አይደሉም። በሌሎች ሀገሮች የሚኖሩ የሐይማኖት ተጋሪወቻቸው ግን አሉ። በዚህም የተነሳ በራሳቸው ሀገር ዜጎች የሀይማኖት ጭቆና እየተደረገባቸው ነው ተብሎ ሲታሰብ ቀድሞ አለሁ የሚል የሌላ አካባቢ ሕዝብና መንግሥት መኖሩ የማይቀር ነው። ለምሳሌ በሀገራችን ታሪክ የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጎን ተሰልፈው ሊዋጉ የቻሉት በቱርክ የሚደገፈውን የግራኝ መሀመድ ጦር ለመመከት ነበር። ኢትዮጵያም ብትሆን በግብጽ የሚኖሩ የኮፕቲስክ ክርስቲያኖች የሀይማኖት ጭቆና ደርሶባቸዋል ብላ ባመነች ጊዜ ዐባይን እገድባለሁ እስከማለት ሄዳ የግብጽን መንግሥት ታስፈራራ እንደነበረ ከታሪክ እንረዳለን። ይህ ሁሉ የሚሆነው ከሀገር ድንበር አልፎ ሕዝቦችን የሚያስተሳስር ገመድ ስላለ ነው።

የርዕዮትአለም አንድነትም ቢሆን ብዙ ሀገሮችን በአንድ የማስተሳሰር ትልቅ አቅም ያለው የማንነት መገለጫ ነው። በኩባ፣ በቬትናም፣ በቺሌ፣ በኮሪያ፣ - - - በተደረጉ ጦርነቶች የርዕዮትዓለም አንድነት አለን በማለት በመንግሥት ደረጃም ሆነ በግለሰብ ውሳኔ ተካፋይ በመሆን መስዋዕትነት የተቀበሉ የውጭ ዜጎች እጅግ ብዙ ናቸው። የሶማሌን ወረራ ለመመከት የየመን፣ ሩሲያና የኩባ ወታደሮች ከኢትዮጵያ ሰራዊት ጎን በመሰለፍ ደማቸውን ያፈሰሱት የርዕዮትዓለም አንድነት (የጋራ ማንነት) አለን በሚል ነበር።

የሰውን ልጅ ሰው የሚያሰኘው በሁሉም ዘንድ የሚታይ የጋራ ማንነት አለው። ደስታን፣ ሀዘንን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን የሚገልጽበት መንገድ፣ የስራ ባህል፣ በዕቅድ የመመራት፣ በቋንቋ የመግባባት ችሎታ፣ የአስተዳደርና የፍትህ ተቋማት አደረጃጀት፣ የንግድና የግብርና ተግባራት፣ የምርምርና የፈጠራ ሥራወች፣ - - - እነሰም በዛም የሁሉም ሰው የጋራ

መገለጫወች ናቸው። ከሌሎች ፍጡራን ጋር የምንጋራቸው ማንነቶች መኖራቸውንም ማመን ያስፈልጋል። ማንኛውም ሰው ከሌላው የሚለይበትም ሆነ የሚጋራው ማንነት አለ። ቋንቋ፣ ቀለም፣ አስተሳሰብ፣ ልማድ፣ - - - የአንድ ግለሰብ/ማኅበረሰብ ማንነት መገለጫወች እንጅ በራሳቸው ማንነት አይደሉም፤ ብቻቸውን ማንነትንም አይገልጹም።

ማንነትን ለማክበር ስንነሳ ከላይ የተጠቀሱትን ዕውነታወች ታሳቢ በማድረግ መሆን ይኖርበታል። የቤተሰብ መብትን ለማስከበር ስናቅድ በቤተሰቡ ውስጥ የሚካተቱትን ግለሰቦች መብት በሚነካ መልኩ መሆን የለበትም። የአካባቢን መብት እናስከብራለን ስንል የግለሰብና የቤተሰብ መብቶችንም ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። የአንድ ሀገር ዜጎችን መብት ለማስከብር ስንታገል የግለሰብ፣ የቤተሰብና የአካባቢ መብቶችን በሚጥስ መልኩ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል። የሰው ልጆችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር፣ በተዋረድ ያሉ ማንነቶችን ማክበርና ማስከበርን ያጠቃልላል። ጎጂ የሆኑ የማንነት መገለጫወች ቢኖሩ እንኳ የሌላውን መብት እስካልነኩ ድረስ በትምህርትና በውይይት ለማስተካከል መጣር እንጂ በኃይል ለማስወገድ መሞከር የህዝቡን መብት መጣስ ይሆናል።

በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ወቅት ኢትዮጵያ በ14 ክፍላተሀገሮች የተከፋለች ነበረች። እኒህ ክፍላተሀገራት በደስታም ይሁን በሀዘን በነበራቸው ተሳትፎ በየራሳቸው ውስጥ የፈጠሩት የጋራ ማንነት አለ። በረጅም ጊዜ ቆይታ ስር እየሰደደ የመጣው አካባቢያዊ ማንነቱ ከጎሳ፣ ከቋንቋና ከሀይማኖት ቀድሞ ሲጠቀስ ኖሯል። ጎንደሬ ነኝ፣ ጎጃሜ ነኝ፣ ወሎየ ነኝ፣ - - - ማለት ለረጅም ጊዜ የኖረና አሁንም ጨርሶ ያልጠፋ አካባቢያዊ ማንነት ነው። ይህ የስነልቦና አወቃቀር ከኢሕአዴግ ወደስልጣን መምጣት በኋላ ቀስ በቀስ እየተሸራረፈ እንዲጠፋ ብዙ ሥራ ተሰርቷል።

ባለፉት 27 አመታት የነበረው ማኅበራዊ አደረጃጀትና የጋራ ማንነት ለማንም የማይገባ ቅጥ አምባሩ የጠፋ ሆኖ እሳካሁን ቆይቷል። ቋንቋን፣ ጎሳን፣ ሀይማኖትን፣ የአስተዳደር አመችነትን፣ ታሪካዊ መሰረትንም ሆነ የሕዝብን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ በወቅቱ ወታደራዊ አቅም በነበራቸው ወያኔና ኦነግ ፍላጎት ብቻ "አንተ ይኸን ያዝ! እኔ ያንን ልውሰድ" ተባብለው ከተከፋፈሉ በኋላ ቀሪውን ደስ እንዳላቸው በመመደባቸው ለማያባራ ብጥብጥና መፈናቀል አጋልጠውናል።

ጉልበት በሚኖረን ጊዜ የምናደርጋቸው ነገሮች የወደፊቱን ታሳቢ ያደረገ ቢሆን ለራስም ለሀገርም ኩራት ነው። ዛሬ አቅም አለን ብለን በማንአለብኝነት የምንፈጽማቸው ነገሮች ቆይተው ማስጠየቃቸው አይቀርም፤ ምክንያቱም ጉልበት ከዕድሜ ጋር የሚያረጅ፣ ማንኛውም ነገር በጊዜ ሂደት የሚለወጥ በመሆኑ ነው። በአሁኑ ወቅት ሁላችንም ከስካር መንፈስ ተላቀን የምናውቀው አደረጃጀት ናፈቀን ብለን መጠየቅ ጀምረናል። ወልቃይቴዎች "እኛ ጎንደሬወች እንጅ ትግሬወች አይደለንም" እያሉ ነው። ራያወች "ወሎየነታችንን መልሱልን" ብለው እየጮሁ ነው። ሲዳማወች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ስር አልጠረነፍም ብሎ በማመጹ በክልል ደረጃ እንዲዋቀር ተፈቅዶለታል። በየአካባቢው የሚነሱ የማንነት ጥያቄወች በጥናት ላይ ያልተመረኮዘው በማንአለብኝነት የተደረገው የተዛባ አከላለል ያስከተለው ውጤት ነው። በሁሉም ክልሎች የሚኖሩ ሕዝቦች በአዲሱ አከላለል ደስተኞች አይደሉም። የአማራ ክልል ብሎ አገውን፣ ቅማንቱን፣ ኦሮሞውን፣ ራያውን፣ ወልቃይቴውን፣ አርጎባውን፣ ወይጦውን፣ ሽናሻውን በስሩ መያዝ ትክክል አይሆንም። ኦሮሚያ ክልል ብሎ በውስጡ የሚኖሩትን ሕዝቦች መብት አልባ አድርጎ መቀጠሉ ፍትሀዊ አይደለም። ሌሎችም ክልሎች የዜጎችን መብት በሚጥስ መልኩ የተዋቀሩ ናቸው።

መፍትሄ የሚሆነው የቀድሞ ማንነቶችን መመለስ ነው። በርግጥ በአዲሱ አከላለል የተጠቀሙ ወገኖችና አጫፋሪወቻቸው ይህን ሀሳብ ተቃውመው መቆማቸው አይቀርም። በየክልሎቹ የሚኖሩትን ዜጎች ድርሻ ወስደው ሌሎችን ተገዥ ያደረጉ ቡድኖች በቃችሁ ሊባሉ ይገባል።

በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ አካባቢ የተነሳው የብሔር ጥያቄ፣ አቀንቃኞችን ጠቅሞ መላው ሕዝባችንን ለከፋ ጥፋት ዳርጓል። አሁን ዋናው የዘር አቀንቃኝ የሆነው ወያኔና የትግል አጋሮቹ ኦነግና ኦብነግ አቅም አልባ ሆነው ከሆነ በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተውን እሳቤ በማስወገድ የቀድሞ ክ/ሀገራቱን እንደ አካባቢ መንግስታት (Regional states) ማቋቋምና የነበራቸውን የየጋራ ማንነቶች መመለስ ያስፈልጋል። በዚህ መልኩ መደራጀት ከመጣ ጎሳን ከጎሳ የሚያጋጭ መሰረታዊ ምክንያት አይኖርም። የዘር ፖለቲካ ከመከሰቱ በፊት በዘራቸው ምክንያት ብቻ ጥቃት የደረሰባቸው ኢትዮጵያዊያን ስለመኖራቸው የሚገልጽ ማስረጃ አልነበረም፤ ወደፊትም አይኖርም።

ባሳለፍናቸው የመከራ ጊዚያት አማራ ተብሎ ለጥቃት የተጋለጠ ሕዝብ እንደነበረ ሁሉም ያውቃል። አማራ ተብሎ በጠላትነት የተፈረጀው ሕዝብ የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎን እና የሰሜን ሸዋን ሕዝብ የሚያካትት በመሆኑ የተከፈተብንን ጥቃት ለመከላከል በተሰጠን አማራነት መደራጀት አስፈላጊ ነበር። ብዙወቻችን ጠላት ተብሎ የተለየው ሕዝብ ራሱን መከላከል እንዲችል መደራጀት አለበት ብለን ስንደክም የነበርነው አማራወች ነን ብለን አምነን አልነበረም። አማራ ናችሁ ተብለን ስለተጠቃን ጥቃቱን ለመመከት የግድ የጥቃት ሰለባወች የሆንን ወገኖች መተባበር ስለነበረብን እንጂ። አሁን ላይ ሁኔታወች እየተቀየሩ እንደሆነ እያየን ነው። አማራ ጠላታችን ነው ብለው በጠላትነት ሲያዩት የነበሩት ሁሉ በሆነው ሁሉ ተጸጽተው ይቅርታ ጠይቀዋል። የኤርትራው ባለስልጣን በአማራው ላይ የጥላቻ ቅስቀሳ ማካሄዱ ትክክል አልነበረም ብለዋል። አዲሱ የሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ ፕሬዚደንት አቶ ሙስጠፋ ሙህመድ ዑመር "ለበርካታ ዓመታት በአማራው

ላይ ስር የሰደደ አሉታዊ ስብከቶች ስለነበሩ፤ የመጀመሪያ ልዑካን ቡድናችንን በቅርቡ ወደ አማራ ክልል እንዲሄድ እናደርጋለን" የሚል መግለጫ ሰጥተዋል። የኦሮሞና የአማራ ወንድማማችነት መልክ እየያዘ ነው።

ትግላችን በዚያው በገዳያችን እና በአስገዳያቻን ኢሕአዴግ ውስጥ ባሉ ሰዎች የተያዘ ቢሆንም እየታየ ነው የሚባለውን ለውጥ በመደገፍ ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ የለውጥ ኃይል ከሚባለው ቡድን ጎን ቆሟል። ይህ የለውጥ ኃይል ቆም ብሎ የዛሬውን የበላይነት ሳይሆን በሰላም የሚያኗኑረንን የወደፊታችንን ሁኔታ ማየት ይኖርበታል። አካባቢያዊ ማንነትን ደፍጥጦ በዕብሪት የተመሰረተው አዲስ ክልላዊ አደረጃጀት እጅግ እየጐዳን ነው። በየክልሉ የተጠቃለሉት አካባቢወች ከአንድነታቸው ይልቅ ልዩነታቸው ጎልቶ ተባብሮ ከመስራት ይልቅ በስልጣን እና በልማት ስራወች የመጓተቻና የሽኩቻ ሜዳወች ሆነው ቀጥለዋል። ምክንያቱ ደግሞ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች ከአሁኑ አንድነት ይልቅ የቀድሞው ልዩነት ከዐዕምሯቸው ሊወጣ ስላልቻለ ነው።

የወልቃይትና የራያ አካባቢወች ወደትግራይ ሲካለሉ ትክክል ነው ብሎ ይከራከር የነበረው የብአዴን ባለስልጣን የጎጃም በአማራ ስም መገዛት ትክክል አይደለም ብሎ ሊያስብ የሚያስችል አመለካከት የሚኖረው አይሆንም። የጎጃም ሕዝብ የስነልቦና ቀውስ እንዲደርስበት የተሰራው ስራ ውጤት አሳይቷል ማለት ከዕውነቱ ማፈንገጥ አይሆንም። ዛሬ ላይ የራሱን መብት ሳያስከብር ስለወልቃይት እና ራያ የሚከራከረው ብዙ ነው። አማራ አንድ ነው እያለ ሲፎክር የሚውለው ወጣት አማራነትን በስም እንጂ በተሳትፎና በጥቅም አይቶ ሊመዝነው አልቻለም። ራስን በራስ ማስተዳደር አለመቻል የፈጠረበት የተለየ ስሜትም ያለ አይመስልም። ይህም ራስን በዝቅተኛ ደረጃ የመመልከትና ሌሎችን ለገዥነት የተፈጠሩ አድርጎ የመውሰድ የበታችነት አስተሳሰብ ፈጥሯል ማለት ይቻላል። በስልጣንም በልማትም ጎጃም ተጎድቷል የሚል ሰው ሲመጣ ነባራዊ ዕውነቱን ገምግሞ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ "ይኸ የጠላት ወሬ ነው፤ የአማራውን አንድነት የማይፈልጉ ሰዎች የሴራ ተግባር ነው" የሚሉ ጎጃሞች መኖር ለሞራል ውድቀቱ ዋና ማሳያ ነው። በአክቲቪስት ነኝ ባዮችና በካድሬዎች እየተሰራ ያለው ዕውነታም ይህን የበታችነት መንፈስ የማስረጽና የማስቀጠል ተግባር መኖሩን የሚጠቁም ነው። አማራ ከሆነ ማንም ቢያስተዳድረኝ ችግር የለውም የሚለው አመለካከት ከማንም በተለየ መልኩ በጎጃሞች ዘንድ ሲደመጥ መሰማቱ የዕውነተኛ ተወላጆቹ ከተሰሚነት ቦታ የመገለል ሁኔታ መኖሩን ያሳያል። ጎጃምን ወክለው በየደረጃው እንዲቀመጡ የተደረጉ ሹማምንቶች ከረር ያለ የመብት እና የልማት እኩልነት ጥያቄ ማቅረብ ያለመቻላቸው ሚስጥር አንድም የማገናዘብ አቅም የሚያንሳቸው፣ ለራሳቸው ብቻ ከማሰብ የዘለለ ሕዝባዊ ወገንተኝነት የሌላቸው ተመርጠው መሾማቸውን የሚጠቁም ሲሆን፣ ሁለትም ቁልፍ የስልጣን ቦታወች ከወከሉት እና ከሚመሩት ሕዝብ አብራክ ባልተገኙ የአካባቢው ልማት በማያስጨንቃቸው ሰዎች መያዛቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑ ነው። ቅማንቶች በአማራ ስም አንጨፈለቅም ብለው እየተሟገቱ ነው። ጎጃሞች ግን በተሰፈረልን ልክ መተዳደሩን መርጠን የተሰጠንን አጀንዳ አራጋቢ ሆነናል።

የወያኔ አከላለል ከፍቅር ይልቅ ቁርሾ የሚተክል እንዳይሆን ያሰጋል። የሚፈራ ስልጣን እና ደጋፊ ያላቸው ወገኖች የሌሎችን ድርሻ ቀምተው ለደቀድሞ አካባቢያቸው ሲያዳሉ እያየን ነው። እንዲህ ያለውን የተዛነፈ ተግባር ለማስቆም እስካልቻልን ድረስ ፍትሀዊ የስልጣን እና የሀብት ክፍፍል ቦታ እያጣ በአንዱ ሀብት ሌላው እየከበረ ልዩነቱም እየሰፋ መሄዱ አይቀርም። በልማት ተጎጅ ከሆኑት ውስጥ የሚመደቡ ትርፍ አምራች አካባቢወች ብዙ ናቸው። በአማራነት ስም የተያዘው ጎጃም አመራሩን ከሌሎች አካባቢ ለመጡ አማሮች አስረክቦ ራሴን በራሴ እያስተዳደርሁ ነው ብሎ እንዲያምን ተደርጓል። በክልል ላይ ያሉት አድራጊ ፈጣሪወች የየራሳቸውን አካባቢ በማልማት ስራ ሲጠመዱ ጎጃም ግን ካለተመልካች ቀርቷል። ውሀ-አጠር በሆኑ አካባቢወች ለግድብና ለውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ከፍተኛ በጀት እየተመደበ እያለ በተቆርቋሪ እጦት ምክንያት በትንሽ ወጪ የመጠጥ ውሀ ማዳረስ በሚቻልባቸው የጎጃም አካባቢወች የሚኖረው ሕዝብ ንጹህ የመጠጥ ውሀ እንዳያገኝ ሆኗል። በጎጃም ምድር የተገነቡ የኤሌክትሪክ ማመንጫወች የሌሎችን እንጀራ እየጋገሩ ለራሳቸው ህዝብ ጀርባ ሰጥተዋል። የከተማና የገጠር መንገዶች ከሌሎች አካባቢወች ጋር የሚወዳደሩ አይደሉም። ጎጃም ላይ ሊገነቡ የታሰቡ ፋብሪካወች እየታጠፉ ወደሌላ አካባቢ እንዲዛወሩ ሲደረግ ቆይቷል። የአማራ ክልል ከተመሰረተ ወዲህ በጎጃምና በሌሎች የክልሉ አካባቢወች የተገነቡ ፋብሪካወችና የተሰሩ የልማት ስራወችን በዝርዝር ብናይ ልዩነቱ ምን ያህል ሰፊ እንደሆነ እንረዳለን። ጎጃም ከአማራ ክልል ያተረፈው አማራ ነኝ ማለትን ብቻ ሲሆን የራስን በራስ የማስተዳደር መብትን እና በራሱ አቅዶ የልማት ሥራ መስራትን ከእነአካቴው ተገፍፏል። እዚህ ላይ አንድ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ አለ። ባህርዳር ላይ የሚደረገው የልማት ስራ የባለስልጣናትን መኖሪያ ከተማ ለመንከባከብ ተብሎ የሚደረግ ነው፤ ባህርዳርን እንደጎጃም ከተማ ሳይሆን እንደጋራ መኖሪያ ከማየት የመነጨ ነው። ማወዳደር ያለብን ከባህርዳር ውጭ ባሉ ከተሞችና አካባቢወች የተሰሩ ሥራወችን መሆን አለበት።

የፍትህ ጉዳይ ስናነሳ አዲሱ ማሸማቀቂያ ከፋፋይ ጎጠኛ የሚለው ፍረጃ ነው። ጎጠኛ እያሉ የሚከሱን የለውጥ ኃይል ነን ባዮች ከልማትና ከዴሞክራሲ አፋትተውን ሲያበቁ፣ ከላያችን ላይ ቁጭ ብለው፣ የእኛን ጭምር እየወሰዱ፣ ጎጣቸውን ሲያለሙ የሚያሳየው ክፍል ዋናው የድራማው ማጠንጠኛ ነው።

የሕዝብ ተቃውሞ የታየ ባይሆንም እንኳ በደቡብ ልጅነት መንፈስ ከጉራጌ ዞን የተመረጠን ሰው የጨንቻ ከተማ ከንቲባ አድርጎ መሰየም፣ በኦሮሞነት መለኪያ ከወለጋ አምጥቶ ከሚሴ ላይ መሾምም ሆነ ከሌላ አካባቢ በመጡ ሰዎች የጎጃም

ወረዳና ዞኖችን በአማራ ስም ማስተዳደር ከንቀት የመነጨ የሙብት ጥሰት ነው። ፍትሀዊ የልማት ተደራሽነት እንዳይኖር የተደረገው ከሌላ አካባቢ በመጡ ሰዎች ስልጣን በመያዙ እና የአካባቢው ልማት ግድ በማይሰጣቸው የራስ ባልሆኑ ሰዎች መተዳደር በመኖሩ መሆኑም መዘንጋት የለበትም። የመልካም አስተዳደር ችግር አለበት የሚባለው የትግራይ ክልል ከሌሎች ክልሎች የበለጠ እንዲለማ የተደረገው በራሱ ሰዎች ስለሚተዳደር ነው።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ግላዊ ነው። በዚህም ምክንያት ለራሱና ለአካባቢው ማድላቱ የሚጠበቅ ነው። ፍትሀዊነትን ለማስፈን የሚያስችሉ ሚዛን የማስጠበቂያ ስራወችን መስራት ካቃተን ተጠቃሚና ተጎጂ መኖሩ የማይቀር ይሆናል። የጎጃም ክልል ይመስረት ስል ምክንያቴ የቀድሞው ጎጃማዊ ማንነት ከአሁኑ የአማራ አንድነት እሳቤ የበለጠ የሚያስተሳስር እና ቤተሰባዊ ስሜት ስለሚፈጥር ነው። አንዳንድ ሰዎች እንዲህ አይነት ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ ማንሳቱ ተገቢ አይደለም ብለው ይከራከራሉ፤ የአማራውን አንድነት ይጎዳል ብለውም ይተቻሉ። የአማራውን አንድነት እንዳይጎዳ በሚል አዴፓ የሰራው ምን ፍትሀዊ ነገር አለ። አዴፓ ጎጃሞችን እያገለለ ያለው አሁንም እኮ ነው። ምን የሚያቀራርብ ስራ ሰራ፤ ካለፈው ስህተት መቼ ተማረ? አድራጊ ፈጣሪወች በዚህ ወቅት ካላስተካከሉ እኛም ካልታገልን ከተጠናከሩ በኋላ እንዴት እናደርጋለን? ከወያኔ ጋር በፍቅር በወደቁበት ጊዜ ፈቅደው የሰጡትን ዛሬ ተቆጨን ብለው በእኛ ደም ሊያስመልሱ፣ ሰዎቻቸውን ሾመውብን ሲያበቁ የእኛንም ሀብት ጨምረው የራሳቸውን አካባቢ ሊያለሙ አይደለም እንዴ እየሰሩ ያሉት! አማራነት መሬታችንን እና መብታችንን አሳጣን እንጂ መቼ ጠቀመን! አከሰረን እንጂ መቼ አትራፊ አደረገን! የአማራ ተከታይ እንጂ መቼ ባለድርሻ ሆንን!

ትውልዱ መንቃት አለበት። ቀያችንን አስረክበን ወደሌላ መሰደድ ተገቢ አይደለም። አሁን ባለው ስሌት ጎጃም የአማራ ሆነ እንጂ አማራ የጎጃም አልሆነም። አማራነት ጎጃሜዎችን የሚያሰባስብ ሊሆንም አይችልም። የጎጃምን ሕዝብ የሚያሰባስበው ጎጃሜነት ብቻ ነው። የሸዋን ሰው በአንድነት የሚያሰባስበው ሸዌነት እንጂ አማራነት አይደለም። ሌላውም በዚሁ መልክ የሚታይ ነው። ለጎጃም አማርኛ ተናጋሪ የጎጃም አገው እና ሌላው የጎጃም ጎሣ ይቀርባል። ጎጃሞች በክፉም በደጉም ያሳለፍናቸው፣ በስነልቦናና በታሪክ የገነባናቸው ጥልቅ ትስስሮች አሉን። ሌሎች አካባቢወችም መታየት ያለባቸው በዚሁ መልኩ ነው።

ቅድመ-ወያኔ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ - - - በሚል ባለመካለላችን ያጋጠመን ችግር አልነበረም። ችግር ሆኖ እስከአሁን ድረስ ለመከራ የዳረገን በወቅቱ ይቀነቀን የነበረው የሶሻሊዝም ርዕዮተዓለም እና ግልጽነት የጎደለው የብሔር ጥያቄ ባልበሰሉ የወቅቱ አፍላ ጎረምሶች ዐዕምሮ ሰፊ ስፍራ ተሰጥቶት ዋና የፖለቲካ ማጠንጠኛ ተደርጎ መወሰዱ ነበር። በደርግም ሆነ ከዚያ በፊት በነበሩት ጊዚያት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመገለል ስሜት ሳይሰማው በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢወች እንደኗሪው ሕዝብ በእኩልነት እየሰራ ሲኖር ነበር። በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተዘዋውሮ ለመኖር የፈጠረበት ችግርም አልነበረም። በቀድሞው ክፍላተ ሀገር አደረጃጀት አካባቢያዊ መንግስታት መመስረታችን በደርግም ሆነ በንጉሱ ጊዜ እንደነበሩት ጊዚያቶች ሁሉ ተዟዙረን መኖርና መስራትን የሚከለክለን አይሆንም። ስለዚህ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግራይ፣- - - የሚለው አደረጃጀት ተቀይሮ ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩባቸው ህብረብሄራዊ አደረጃጀቶች የጎንደር፣ የወሎ፣ የሸዋ፣ - - - መንግስት በሚል መልክ ማዋቀሩ ጠቃሚ ይሆናል።

የፖለቲካ ቁማርተኞች ከሕዝብ ጫንቃ ይውረዱ!

የሕዝብ መብት ይከበር!

በዜጎች ላይ ግፍ የፈጸሙ ሁሉ ለፍርድ ይቅረቡ!

የተዘረፈ የሀገር ሀብት ይመለስ!

ትንሳኤ ለኢትዮጵያ!